# ፅንፈኛ ፖለቲከኞችና የጥገኝነት አባዜያቸው

ሂሩት ተሻለ 1/15/13

"የሰው ወርቅ አያደምቅ" ይላል የአገራችን አርሶ አደር– የራስ ባልሆነ ወርቅና ጨርቅ መድመቅ የማያኮራ፣ የሰው ነገር ሁሌም የሰው ፣ እንዲያውም የማታ ማታ የሃፍረት ሸማን ማከናነቡ የማይቀር መሆኑን ለማመላከት ሲፈልግ፡፡ መቼም ይህ የሀገራችን ታታሪ አርሶ አደር ይትብሃል ብዙ ነገር ሊያጫውተን ይችላል።

እርግጥ ዛሬ ላይ "ጉራ በኪሱ" የሚል ተቀጥያ ስም የወጣላቸው አንዳንድ ስራ የማይወዱ አሊያም የወንጀል ሱስ የተጠናወታቸው ወገኖች "ምነው ፈጣሪዬ እዚህ አገር ሰው ሆኜ ከምወለድ አሜሪካ ዛፍ ሁኜ በበቀልኩ!" ለማለት የሚዳዳቸው አወቅን ባይ "ጉደኛ ዘመነኞች" ሳያጋጥሟችሁ አይቀሩም፡፡

አዎ! ግና ምስጋና ለልማታዊውና ዴሞክራሲያዊው መንግስታችን ይግባውና እዚሁ ስንት የሚሰራ ነገር እያለ ባህር ማዶን እንደ ማምለጫ አሊያም እንደ ወንጀል መሸሸጊያ በመጠቀም ኢትዮጵያዊንና ኢትዮጵያዊነትን ለማዋረድ የሚከጅላቸው ዘመነኛ መሳዮችን፣ በሌላው ወርቅ አምረውና ደምቀው ለመታየት የሚቋምጡትን ጉደኞች ቤቱ ይቁጠራቸው፡፡

ውድ አንባቢዎቼ እነዚህ የራሳቸውን ወርቅ ጥለው በሰው ወርቅ ለመድመቅ የሚከጅሉ ወገኖችን ለጨዋታ ያህል አነሳኋቸው እንጂ፣ የፅሑፌ ዋነኛ ዓላማ በአክራሪ ኒዮ- ሊብራሎች ፈረስ ላይ እየተፈናጠጡ ኢትዮጵያን ለማተራመስ የሚያቀነቅኑ ፅንፈኛ ፖለቲከኞች ፈውስ ያጣውን የጥገኝነት በሽታቸውን ለማሳየት ነው፡፡

ማስተዋል የሚባል ነገር ያልፈጠረባቸው እነዚህ አክራሪ ፖለቲከኞች ከኢትዮጵያ ጋር ምንም ዓይነት ነባራዊ ሁኔታ የሌለውን የኒዮ- ሊበራሊዝም ስርዓት ገቢራዊ ለማድረግ የሚያከናውኑት ሴራቸው እንደ ዘወትር ፀሎት ሊቆጠር ይችላል፡፡ ታዲያ ፅንፈኞቹ የዚሁ አክራሪ የኒዮ- ሊብራል ስርዓት አጨብጫቢ በመሆን በሰው ወርቅ የመድመቅ አባዜያቸውን በአንክሮ ለሚያጤነው ሰው በእጅጉ ግራሞትን ያጭራል፡፡ ባህር ማዶ ቁጭ ብለው የሚያስደምጡን መሪ መፈክርም በቅጡ የማያወቁትን የኒዮ- ሊብራሊዝም ቅንጭብጫቢ ሃሳቦችን እየገጣጠሙ ማውራት ነው፡፡

በወንጀል የሚፈለጉ ፅንፈኞች ፣ የቀድሞው ስርዓት ናፋቂዎች፣ የሀገራችን ጠላት የሆነው የኤርትራ መንግስት ተላላኪዎች እንዲሁም ከእንቅልፋቸው ብንን ሲሉ ኢትዮጵያ ተበታንና የምትታያቸው አንዳንድ ሟርተኞች በሚሰበሰቡባት ሀገረ- አሜሪካ አሊያም ሌላ ሀገር ውስጥ ሆነው የሚሰጥዋቸው መሰረተ- ቢስ አስተያየቶች፤ ቁም ነገር አልባ ከመሆናቸው ባሻገር የኮሜዲያንነት ባህሪይን እየተላበሱ መጥተዋል፡፡

ታዲያላችሁ ውድ አንባቢዎቼ እነዚህ ፖለቲካን የማያውቁ አሊያም ፖለቲካውን ገና ዳዴ እያሉ የሚገኙ ፅንፈኛ ፖለቲከኞች፡ በሀገረ- አሜሪካ የሚገኙ አንዳንድ የእምነት ተቋማትንና የንግድ ቦታዎችን በፖለቲካ ስም እየፈረጇቸው መሆኑን ብትሰሙ ከቶ ምን ትሉ ይሆን?–አዎ! ወጉን ያጫወተኝ ለአስራ አምስት ዓመታት አሜሪካ የኖረ አንድ ወዳጄ ሲሆን፤ የወዳጄን ጨዋታ በብዕሬ እንዲህ እንደወረደ አቀርበዋለሁ ፡፡...

...አክራሪ ፖለቲከኞቹ በአንድ የእምነት ተቋም አሊያም የንግድ ቦታ ተቀጣጥረው ለመገናኘት ከፈለጉ፤ በዚሁ ሁናቴ ቀጠሮ መያዛቸው አይቀርም፡፡ ታዲያላችሁ እኔም “በምን መልኩ” ማለቴ አልቀረም፡፡ ወዳጄም ለጠቀና ... ይኸውልህ በሀገረ- አሜሪካ አንድ ስቴት ሁለት የቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ያለ እንደ ሆነ ... ጓድ የት እንገናኝ? የቅንጅቱ ወይስ የኢህአዴግ? በማለት ቀጠሮ ይይዛሉ።

ይህ ብቻም አይደለም። ንግድ የሚጧጧፍበት ቦታ ለመገናኘት ከፈለጉም በተመሳሳይ መልኩ ቀጠሮ መያዛቸው አይቀርም። እርግጥም ጉዳዩ ያስገርማል። እነዚህ ወገኖች በሰለጠኑት ዓለም እየኖሩ ኃይማኖትን እና ፖለቲካን ንግድን እና ፖለቲካን ለይተው የማያውቁት አክራሪ ኃይሎች ናቸው። እኔን የደነቀኝ እና ያልገባኝ ጉዳይ ግን የእምነት ተቋማት እና የንግድ ቦታዎች በፖለቲካ ስም መሰየም ያስፈለገበት ምክንያት ነው፡፡ ግና እነዚህ ሃይሎች በኃይማኖትን ጨምሮ በእያንዳንዱ ጉዳይ ሽፋን ፖለቲካዊ አጀንዳቸውን ለመፈፀም የማይቀነጥሱት የቅጠል ዓይነት እንደሌለ ስለሚታወቅ ነገረ-ስራቸው እምብዛም የሚደንቅ አይደለም፡፡

ፅንፈኞቹ ለሀገር የሚመኙት ምርጥ እቅድ እና ፕሮግራም፣ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ መንደፍን ሳይሆን ብሔርን እና ኃይማኖትን ከለላ በማድረግ ሁከት እና ብጥብጥ ማስነሳት እንዲሁም በድህነት የምትማቅቅ ሀገርን መፍጠር ነው፡፡ እርግጥም እንደ እነርሱ እሮሮ እና እንደ እነርሱ እርግማን ይህቺ ሀገር ድሮ ነበር ሊያበቃላት የሚችለው፡፡ ነገር ግን ሀገራችን የህዝብን ኑሮ በተጨባጭ በመለወጥ ላይ የሚገኝ መንግስት የታደለች እንዲሁም ባህር ማዶ ቁጭ ብሎ ለሚቀነቀን ተራ ወሬ ጆሮውን የሚያውስ ህዝብ የሌለባት በመሆኗ ፍላጎታቸው በረሃ ላይ እንደተዘራ ዘር መክኖ እየቀረ ነው፤ ወደፊትም መምከኑ አይቀሬ ነው።

የፅንፈኞቹ ጉዳይ በዚህ ብቻ ተዘርዝሮ የሚያበቃ አይደለም። እነዚህ ሃይሎች ከአክራሪ ኒዮ ሊብራል ኃይሎች ጋር እጅ እና ጓንት ሆነው በማቀንቀን ነውጥ ለማስነሳት የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም፡፡ አክራሪ ፖለቲከኞቹ የክፋት ካባቸውን ደርበው፣ አስበውና ቀምረው ተላላኪ ሆነው ቢንቀሳቀሱም፤ ይህን እኩይ ተግባር መቀበል የሚችል ሕዝብ እንደሌለም የተረዱ አልመሰለኝም፡፡

ያም ሆነ ይህ አብዛኛዎቹ አክራሪዎች የሚቀምሩት የጥፋት ተልዕኮ እዚህ ሀገር ቤት አልሳካ ሲላቸው የመጨረሻ ምሽጋችን ናት ወደሚሏት ሀገረ አሜሪካ ሲፈረጥጡ ይስተዋላሉ፡፡ ከእነዚህ ፅንፈኞች ውስጥ "በድንገቴ" ፖለቲከኝነታቸው የሚታወቁት ዶክተር  ፍሰሃ እሸቱ አንዱ ናቸው። እኚህ ሰው በብርሃን ፍጥነት ከዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ባለቤትነት ወደ ፖለቲከኝነት የተቀየሩ ናቸው—ለዚያውም ሀገራችንን አሁን ካለንበት ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ ወደ ድህነት ድቅድቅ ጨለማ ጉዞ ሊያሻግሩን ያቆበቆቡ ፅንፈኛ። መቼም "ልብ እንቅርትን ይመኛል" ከማለት በስተቀር የፖለቲካውን ሀሁ ቆጣሪ ግለሰብ ምንም ልንላቸው እንችልም።

በራሳቸው አንዳችም ዓይነት ፖሊሲና ስትራቴጂ የሌላቸው ፅንፈኞች ሌላው ቀርቶ ለሀገራቸው በጎ የማያስቡ ናቸው። እነዚህ ሃይሎች እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ "ኢትዮጵያን አትርዱት" የሚል መርህ አንግበው ሲንቀሳቀሱ በገሃድ ተመልክተናቸዋል፡፡ እናም በአንድ ወቅት "በኢትዮጵያ ያከናወንነው የፖለቲካ ስልት /የነውጥ አካሄዳቸውን ማለታቸው ነው/ ያልተሳካልን በትምህርት ስላልበቃን ነው" ሲሉ የተደመጡበት ጊዜም ነበር ፡፡

ታዲያ እነዚህ ፅንፈኞች አሜሪካ የሚገኙ ዲያስፖራዎችን የእነርሱ ተከታይ ለማድረግ ብሎም እርጥባን ለመለመን በአምሳያ ሚዲያቸው የማይቀባጥሩት ነገር የለም፡፡

እናም እዛው ባህር ማዶ ተቀምጠው የመንግስትንና የህዝቡን መልካም ስም ለማጉደፍ የማያኸጎደጉዱት የወሬ ጋጋታ የለም፡፡ ምን አለፋችሁ—ሲያሻቸው እስከዚህም ድረስ ከመሄድ የሚቦዝኑ አይደሉም።… በአሜሪካ ሆሊውድ በተሰኘ የፊልም ኩባንያ ውስጥ  የሚፈበረኩ "ሆረር" የተሰኙ አስፈሪ እና እርስ በርስ የመበላላት ድራማዊ ትዕይንትን ከሚያሳዩ ፊልሞች ጋር በቀጥታ በማዛመድ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ስርዓትም ልክ እንደ ፊልሙ ሕዝቡን እርስ በርሱ እንዲበላላ እያደረገ ነው ሲሉ የመወትወታቸው ጉዳይ አስገራሚ እና ሰበካቸውም አስቂኝ ነው። ገና ለገና ውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ ስለ ሀገሩ በቂ ግንዛቤ የለውም የሚል የእውር ድንብር እሳቤን ይዘው ፡፡

ይሁንና አብዛኛው ዲያስፖራ አሁን፣አሁን እያወቃቸው በመምጣቱ "ዓይናችሁን ለአፈር" እያላቸው ነው፡፡ ነገር ግን ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደሞከሩት ጥቂት በወንጀል ድርጊት የሚፈለጉና የቀድሞው ስርዓት አቀንቃኝ የሆኑ ግለሰቦች ዓይናቸውን በጨው ታጥበው ሀገራችን ወስጥ ያለውን ዕውነታ ገልብጠው በማሳየት "እኛን ብቻ ስሙን" ማለታቸው አልቀረም፡፡

የዲያስፖራው ፅንፈኞችም ይሁን በሀገር ውስጥ ለስሙ ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን አክብረን እንንቀሳቀሳለን የሚሉት አንዳንድ ፅንፈኛ ተቃዋሚዎች ከሚያመሳስላቸው ጉዳዩች ውስጥ አንዱ ሁለቱም የሁለት ዓለም ሰዎች መሆናቸው ነው፡፡ የሀገር ውስጡን ተቃዋሚ ለአብነት ያህል ብናነሳው እንኳን፤ አንደኛው የፖለቲካ ፖርቲ ከሌላኛው ጋር ቢዋሃድም ከሌላኛው ጋር በምንም የፖለቲካ አቅጣጫና ርዕዩተ-ዓለም አይገናኝም፡፡

እርስ በእርሳቸው ለዓመታት እየተነቋቆሩ ሲጐነታተሉ ይኖሩና ምርጫ በመጣ ጊዜ እንደምንም ገገርውን ፖርቲ ለመጣል አንድ ላይ ለመሰባሰብ ይሞክራሉ፡፡ ግና የፖለቲካ አጀንዳቸው ሲፈተሽ ሆድና ጀርባ ናቸው፡፡ ስብስቡ በምን ዓይነት የፖለቲካ አጀንዳ ሀገርን እንደሚመራ እነሱን አያስጨንቃቸውም– ብቻ ሩጫቸው ሁሉ ስልጣን የተባለውን የህልም ዓለም ፍቅረኛቸውን መጨበጥ ብቻ ነው።

ምናልባትም ግድ ሆኖባቸው በምርጫ ሰሞን በአንድ እጅ እናጨብጭብ ቢሉ እንኳን ምርጫ ከተጠናቀቀ በኋላ ግን እምጥ ይግቡ ስምጥ የሚገቡበት ጉድጓድ አይታወቅም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሚያራምዱትን ፖለቲካ ያየን እንደሆነ እርስ በእርሱ የሚጣረስ ነው፡፡ በምርጫ የምረጡኝ ቅስቀሳ ወቅት ሕዝብን ሲቀሰቅሱ ልብ ያለ ሰው በሁኔታቸው ሊገረም ይችላል፡፡ ለአብነት ያህል አንደኛው የፖለቲካ ፖርቲ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች መብት ሳይከበር የኢትዮጵያ አንድነት መከበር አለበት ብሎ ሲነሳ፤ ሌላኛው ደግሞ የቡድን መብት ሳይሆን፣ የግል መብት ነው ኢትዮጵያ ውስጥ መጀመሪያ መከበር ያለበት በማለት አካኪ ዘራፍ ይላል፡፡ እንግዲህ እንዲህ ዓይነቱ የተዘበራረቀ የአታሞ ስልተ-ምት ያለው ቅስቀሳ ተጣምረናል በሚሉ ፖርቲዎች ውስጥ የሚከናወን አስቂኝ ድራማ መሆኑን ውድ አንባቢዎቼ ልብ ይሏል!

ታዲያ እዚህ ላይ አስገራሚው ነገር እነዚህ ወገኖች ስለ የቡድንና የግል መብቶችን አስመልክቶ በኢፌዴሪ ህገ-መንግስት ላይ የሁለቱም መብቶች ዋስትና ማግኘታቸውን የተደነገገውን ዕውነታ ሳያውቁ በደፈናው የሚያደርጉት ጉንጭ አልፋ ክርክር ነው። ብቻ ምን አለፋችሁ!... ሌላም አስገራሚ ጉዳይ ደግሞ በጥምረቱ ውስጥ የሚገኘው አንዱ ፓርቲ ህገ-መንግስቱ ያሰፈረውን የመሬት መሸጥ መለወጥ የለበትም ድንጋጌን ሲደግፍ፤ ሌላኛው ደግሞ በተራው ይፃረራል፡፡

ምልከታችንን ወደ ውጭው ፅንፈኛ ስንመለስ ደግሞ፤ እንደ ሀገር ውስጦቹ ተቃዋሚዎች ሳይሆን እነዚህኛዎቹ የአክራሪ ኒዮ ሊብራል ደቀ-መዝሙር ሆነው የሚሰሩት በግላጭ ነው። እንዲያውም ለፈጠሯቸው የዜና አውታሮች ዋነኛ የወሬ ምንጭ አድርገው አክራሪ ኒዩ-ሊበራል ሃይሎችን በመጠቀም የገዛ ሀገራቸውን ስም ያጠፋሉ፤ያስጠፋሉ። የኒዩ-ሊበራል ተከታይ መስለው በመታየትም ከእነሱ የሚሰጣቸውን የዶላር ጉርሻ እየተጠቀሙ በህ-መንግስታዊ ስርዓቱ ላይ አደጋ ለመፍጠር የማይቆፍሩት ጉድጓድ የለም፡፡

ፅንፈኞቹ በሀገራችን አመፅ ተቀጣጥሎ በስርዓቱ ላይ አደጋ እንዲፈጠር ለማስቻል ከሚጠቀምባቸው መሳሪያዎች ውስጥ የወሬ ምንጮቻቸውን፣ የፕሬስንና የድረ-ገጽ አብዮቶቻቸውን በጥቂቱ መጥቀስ ይቻላል፡፡ በቀዳሚነትም የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ/ በዋነኛነት የአማርኛው ክፍል/ እና ኢሳት የተሰኘው የግንቦት ሰባት ጣቢያ ዋነኛዎቹ የነውጦች ማቀጣጠያ ማሽኖች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ፅንፈኞቹ በአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ በየእለቱ ብቅ እያሉ ፖለቲካዊ ትወናቸውን ሲያከናውኑ መደመጡ የተለመደ ነገር ነው፡፡በዚሁ ሬዲዮ ጣቢያ ሁሉም አክራሪ ፖለቲከኞች ወረፋቸውን እየጠበቁ በመፈራረቅ የውሸት ፕሮፖጋንዳቸውን ሲደሰኩሩ ማድመጥ አደስ ክስተት አይደለም፡፡

ጋዜጠኞቹም ቢሆኑ የጋዜጠኝነት ስነ-ምግባሩን ባልተከተለ መልኩ አብረው ከእነሱ ጋር እጅ እና ጓንት በመሆን ሲለፍፉ ያመሻሉ፡፡ ወሬያቸው ሁሉ በመጥፎ ጉዳይ ላይ ያተኮረ እንጂ አንዳችም በጎ ነገር የሚደመጥበት አይደለም፡፡ በእነርሱ "የአናክሰው" ፕሮፖፋንዳ ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ሕዝቡ የብሔር ጥያቄ አስነስቶ አመፅ አከናውኗል ካሉ፣ ነገ ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የእስልምና እምነት ተከታዮች እርስ በርሳቸው አሊያም ከሌላው እምነት ጋር ምንትስ ሆነ የሚል የበሬ ወለደ ድርሰታቸውን ያራግባሉ፡፡

ታዲያ ለሚያነሱት የበሬ ወለደ ፕሮፖጋንዳ ለምስክርነት በሬዲዮ ጣቢያ የሚቀርቡት ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉና በውጭ የሚገኙ ጽንፈኞች ናቸው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም። አሁን በተጨባጭ በኢትዮጵያ ውስጥ መጥፎ ሁኔታ እንዳለ አስመስለው በስልክ አስተያየት የሚሰጡ ደምበኞችም አሏቸው፡፡ ልብ ብለን የስልክ መልዕክቱን ያደመጥን እንደሆነ እነዚህ አስተያየት ሰጪዎች ድምፃቸውን እየለዋወጡ የሌሎች ሰዎችን በማስመሰል ድራማዊ ትዕይንትን ያቀርባሉ፡፡ መልዕክቱን ሁሌ የሚጀምሩት ደግሞ በአንዲት ቃል ነው። ይኸውም (Hello VOA) "እንደምን ናችሁ ቪኦኤዎች እከሌ ነኝ" በሚል። ከዚያም በሬድዮ ጣቢያው በሉ የተባሉትን የቅጥፈት ወሬ ያንበለብሉታል።…

ፅንፈኛ ፖለቲከኞቹ የሚጠቀሙበት ሌላኛው ጣቢያ ኢሳት ነው፡፡ በጣቢያው የማይባል ነገር የለም። በርካታ የውሸት ርእሰ ጉዳዮች እየተነሱም ሀገር የፈራረሰ ያህል ሲወራም ሃፍረት የላቸውም። የቪኦኤ ጋዜጠኞች የቀድሞው ስርዓትና የኢህአፓ ርዝራዦች ሲሆኑ፤ እነዚህኛዎቹ ደግሞ ሀገር ቤት በፈፀሙት የሙስና ቅሌት ምክንያት ምንም ሳይባሉ በርግገው አሜሪካ የገቡ ናቸው።

ሌላው ቀርቶ አስመራ የሚገኙት የአቶ ኢሳያስ የሚዲያ አውታሮችም የእነርሱ መልዕክት ማስተላለፊያ ናቸው፡፡ ምክንያቱም የአስመራው መንግስት ኢትዮጵያን ሊበታትን ይችላል የሚል

ርዕሰ ጉዳይ ካገኘ ወደ ኋላ ስለማይል አስመራ ድረስ መጥተው ፅንፈኛ ፖለቲከኞች የፈለጉትን እንዲሉ ከአቶ ኢሳያስ ፍቃድ ስለተሰጣቸው ነው፡፡

በኤርትራ ድምፅ ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን ስርጭት አቶ ኢሳያስ ብቻ ሳይሆኑ ልክ እንደ አቶ ኢሳያስ እንዲያውም እነሱ ራሳቸው ኢትዮጵያውያን ሆነው ፀረ-ኢትዮጵያ አጀንዳ የሚያራምዱ አክራሪ ፖለቲከኞችም በተደጋጋሚ ቃለ-ምልልስ ያደረጋሉ፡፡ የግንቦት ሰባት መሪ ነኝ ባዩ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋና ሌሎች የኦነግ አመራሮችም የዚሁ ኮሜዲ ድራማ አካል ናቸው ፡፡

እንግዲህ አስቡት ትላንት የሀገራችን ሉዓላዊነት በአደባባይ ከደፈረ ጠብ አጫሪ መንግስት ሚዲያን በመጠቀም የገዛ ወገናቸውን አንድነት ለመበታተን፣ ሰላሙን ለማደፍረስ እና ልማቱን እንዲቀለበስ ደፋ ቀና የሚሉት እነዚህ ፅንፈኞች፤ ምን ያህል የሀገራችን ደመኛ ጠላት መሆናቸውን መገንዘብ ያሻል፡፡ እነዚህ ሃይሎች የህገ-መንግስት የበላይነት፣ የሀገር ሉዓላዊነት እና የህዝብ ጥቅም ብሎም ክብር የሚባሉ ነገሮችን አያውቁም፡፡ የእነሱ የፖለቲካ ስልት ማጠንጠኛ አመፅ ለማቀጣጠል እየጣሩ ስለ ዴሞክራሲ ይሰብካሉ፤ ስለ ድህነትና ደም መፍሰስ እየተመኙ ስለ ሀገር ዕድገት እና ሰላም አፋቸውን ሞልተው ይናገራሉ፡፡ ቅጥ አምባሩ የጠፋው የፖለቲካ ስሌት።

ፀረ-ሀገር እና ሕዝብ ጥላቻቸው ወሰን የለውም፡፡ የሀገራችን የእድገት ጉዞ ለመቀልበስ የአክራሪ- ኒዮ ሊበራል ሃይሎችን በር እያንኳኩ በገሃድ ለኢትዮጵያ ብድርና እርዳታ እንዳይሰጥ ይከሳሉ፡፡ ከዚህ ባሻገርም በሀገራችን መንግስትና በታታሪው ሕዝቡ ርብርብ እየተከናወኑ የሚገኙ ተጨባጭ የልማት ስራዎች እንዲቆሙ የማያደርጉት ጥረት የለም፡፡

በመንግስት እና በሕዝብ ተሳትፎ እየተከናወነ ያለውን ታላቁን የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ እንዲሰናከልም ብዙ ጥረዋል፡፡ እነዚህ ኃይሎች አክራሪ ሊበራል ሃይሎችን በማነጋገር ኢትዮጵያ እያከናወነች ያለው የህዳሴ ግድብ በቀጣናው ሃገራት ላይ ችግር ፈጣሪ ስለሆነ መቆም ይገባዋል ሲሉም ይከሳሉ፡፡ እንደ  ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ዓይነት ጽንፈኞች የዚህ ድራማ ሁነኛ ተዋናይ እንደነበሩ መዘንጋት አይገባም፡፡

በጥቅሉ አክራሪ የፖለቲካ ጽንፈኞች በወገን ላይ ሴራ በመቀመር ረገድ የተጠናወታቸው በሽታ በቀላሉ የሚለቃቸው አይመስልም፡፡ እነሱ የሚያራምዱትን የዜሮ ድምር የፖለቲካ ስልት ሕዝቡ ተሰላችቶ አንቅሮ እንደተፋውም ገና አልገባቸውም፡፡ያም  ሆነ ይህ የኢትዮጵያ ሕዝብ አሁን በሀገሪቱ የተገኘውን ሰላም እያስጠበቀ፣ የልማት ዕድገቱን በማስቀጠል የሀገሪቱን ህዳሴ ለማረጋገጥ ደፋ ቀና እያለ ነው።፡፡ ላለፉት ዘጠኝ ተከታታይ ዓመታት የተመዘገቡት የልማት ውጤቶችም የዚሁ ወጤቱ ማረጋገጫዎች ናቸው፡፡

ሆኖም ፅንፈኞቹ በጥገኝነት አባዜያቸው እየተመሩ በሰላማዊ የትግል ስልት ስልጣን ማግኘት ስለማንችል ያለን አማራጭ ነውጥን በማቀጣጠል በኃይል ስልጣንን መቆናጠጥ ነው ብለው የሚያስቡ ከሆነ፤ በዓለም ላይ ያለውን ትልቁን ስህተት በእርግጥም መሳሳታቸውን አስረግጬ ልነግራቸው እወዳለሁ። ምክንያቱም እንደ ትላንቱ ሁሉ ዛሬም ህግን እየተላለፉ በሀገሪቱ ላይ አደጋ ሲፈጥሩ ቆሞ የሚመለከት ህገ-መንግስታዊ ሥርዓት ኢትዮጵያ ውስጥ ስላልተዘረጋ ነው፡፡ ቸር እንሰንብት፡፡